# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ

## የዓቢይ ጾም አራተኛ «መፃጉዕ» ይባላል።

ይህ ዕለት የዓቢይ ጾም አራተኛ ሰንበት ነው። ስሙም እንደ ቅዱስ ያሬድ የዜማ ስያሜ «መፃጉዕ» ይባላል። በዚህ ዕለት ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሽተኞችን ስለማዳኑ ታአምራትን ስለማድረጉ ጎባጣዎችን ስለማቅናቱ ለምጻሞችን ስለማንጻቱ ስለ መለኮታዊ ማዳኑ እና ታምራቱ ይመለካል። «መፃጉዕ» ማለት በደዌ ዳኛ በአልጋ ቁራኛ የተያዘ በሽተኛ ማለት ሲሆን ቅዱስ ያሬድ በክርስቶስ ስለተፈወሱ ሰዎችና ስለክርስቶስ ፈዋሽነት የዘመረው የመዝሙሩ መክፈቻና ርዕስ በመሆኑ እለቱ «መፃጉዕ» ይባላል።

### የዕለቱ ምስባክ

እግዚአብሔር ይረድኦ ውስተ ዐራተ ሕማሙ
ወይመይጥ ሎቱ ኩሎ ምስካቢሁ እምደዌሁ
አንሰ እቤ እግዚኦ ተሣሃለኒ

እግዚአብሔር በደዌ አልጋ ሳለ ይረዳዋል
መኝታውንም በበሽታው ጊዜ ያነጥፍለታል
እኔም አቤቱ ማረኝ እልሃለሁ።

*መዝ ፵፤፫-፬*

**ወንጌል፥** ዮሐ ፭፤፩-፳፭
**ቅዳሴ፥** የጌታችን ቅዳሴ (ነአኲተከ)

### የዕለቱ የቅዱስ ያሬድ መዝሙር ርዕስ

አምላኩሰ ለአዳም (የአዳም ፈጣሪው)

### በቅዳሴ ሰዓት የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች

| | ንባብ | አንባቢ |
|---|---|---|
| 1 | ገላ ፭፤፩ እስከ ፍጻሜው | ዲያቆን (ገባሬ ሰናዩ) |
| 2 | ያዕቆ ፭፤፲፬ እስከ ፍጻሜው | ዲያቆን (ንፍቅ ዲ.) |
| 3 | የሐዋ ሥራ ፫፤፩-፲፪ | ረዳቱ ቄስ (ንፍቅ ካህን) |

### የዕለቱ ትምህርት

## በሰንበት ለበሽተኞች ዕረፍትን ሰጠ

በዚህ ዕለት ቅዱስ ያሬድ መድኃኒታችን በዕለተ ሰንበት የፈወሳቸውን ልዩ ልዩ ሕሙማንን እያስታወሰ ሕይወትና መድኃኒት በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ዳኑ፣ ተፈወሱ እያለ ይዘምራል። በመዝሙሩም «አምላኩሰ ለአዳም ለእረፍት ሰንበተ ገብረ - የአዳም አምላክ ሰንበትን የፈጠረው (የሠራው) ለእረፍት ነው።» ስለዚህ በሰንበት ዕውራን እንዲያዩ ማድረጉ፤ ጎባጣዎችን ቀንተው እንዲሄዱ በማድረግ ማሳረፉ፤ በአልጋ ቁራኛ፤ በደዌ ዳኛ የተያዙትን በመፈወስ ማሳረፉ፤ እጃቸው የሰለለውን የሰለለ እጃቸውን ማቅናቱ እኮ የአዳም አምላክ ሰንበትን ለእረፍት ስለፈጠራት ነው። ይህንን በማድረጉም ሰዓሬ ሰንበት ሊባል አይገባውም። «እግዚአ ሰንበት - የሰንበት ጌታ» ሊባል ይገባዋል እንጂ ብሎ አይሁድን እየወቀሰ መሲህን እየቀደሰ ሰንበትን እየተረጎመ እና እያኩነሰነሰ መድኃኒታችን በዕለተ ሰንበት ያደረጋቸውን ታምራት እያስታወሰ ይዘምራል።

ጥቅስ በግዕዝ፥ *በሰንበት ፈወሰ ዱያነ ወከሰተ ዐዕይንተ ዕውራን፤ በሰንበት ፈድፋደ ከያነ አፍቀረነ ሰርአለነ ሰንበተ ለእረፍት።*
ትርጉም፥ በሰንበት ድውያንን ፈወሰ የዕውራንን ዓይኖች ገለጠ፤ በሰንበት አብዝቶ ወደደን ሰንበትንም ለዕረፍት ፈጠረልን ይላል።

የመቶ አለቃውን ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ የፈወሰው በሰንበት ነው ብሎ ቅደስ ያሬድ ዘምሯል።

ጥቅስ በግዕዝ፥ *«ይቤሎ መስፍን ለኢየሱስ ክርስቶስ በዕለተ ሰንበት ኢይደልወኒ ከመአንተ ትበእ ታህተ ጠፈረ ቤትየ አዝዝ በቃልከ ወየሀዩ ወልድየ»*
ትርጉም፥ መቶ አለቃው ኢየሱስን በዕለተ ሰንበት ከቤቴ ጣራ በታች ልትገባ አይገባኝም በቃልህ እዘዝ ልጄም ይድናል» አለው ብሎ ልጁን በሰንበት እንደፈወሰው ተናገረ (አምላኪየ) ማቴ ፲፭፤፳፩-፳፰

እውራንንም ስለማብራቱ ሊቁ *«ከልሐ ዕውር በውስተ ፍኖት ወገሰጽዎ እለ ይመርህዎ ከመያርምም ወአበየ ከልሐ እንዘይብል ተሣሃለኒ እግዚእየ ወልደዳዊት»* ሲፈታ «እውሩ በመንገድ ላይ አሰምቶ ጮኸ፤ የሚመሩትም ዝም ይል ዘንድ ተቆጡት እርሱ ግን እንቢ ብሎ የዳዊት ልጅ ሆይ እርዳኝ ብሎ ጮኸ» ማለት ነው ብሎ ዘመረ (ማቴ ፳፤፳፱-፴፬)

*መፃጉዕም በሰንበት ስለመፈወሱ እንዲህ ብሎ ቅዱስ ያሬድ ጮኸ።*

ጥቅስ፥ *«አህየዎ ኢየሱስ ለመፃጉዕ በዕለተ ሰንበት* - ኢየሱስ በዕለተ ሰንበት መፃጉዕን ፈወሰው» አለ (ሐዐቦሙ)

የዕውሩን ዓይን በዕለተ ሰንበት እንዳበራለት ሲናገር እንዲህ አለ።
ጥቅስ፥ *«በሰንበት ገብረ-ተአምራተ ወረቀ ምድረ ወገብረ ፅቡረ እህየወ እውረ በሰንበት»*
ትርጉም፥ «በሰንበት ተአምራትን አደረገ መሬት ላይ እንትፍ አለ ጭቃም አዘጋጀ ዕውሩንም በሰንበት አዳነ» ብሎ ዘመረ (ዮሐ ፱)

እጁ ሽባ ሆኖ የነበረውን ሰውም በሰንበት ፈወሰው ይላል ቅዱስ ያሬድ፥

ጥቅስ፥ *«ሖረ ኃቤሁ ዘየብበሰት እዴሁ ወፈወሶ በዕለተ ሰንበት ወይቤሎ ተሐደገ ለከ ኃጢአትከ ዑቅ ኢተአብል»*

ትርጉም፥ እጁ የሰለለበት ሰውም ወደ ኢየሱስ ሄደ በሰንበት ፈወሰው ኃጢአትህ ተሰረየችልህ ሁለተኛ እንዳትበድል እወቅ አለው ብሎ ዘመረ። ስለመፃጉዕም፥

ጥቅስ፥ *«በሰንበት ተራከቦ ኢየሱስ ለመፃጉዕ ወይቤሎ ተንስእ ወንሳእ አራተከ ተኃድገ ለከ ኃጢአትከ ዑቀ ኢተአብስ እምዝ ከመዘየአኪ ኢይርከብከ ተንሢአ ነሥአ አራቶ አተወ ቤቶ ውእቱ መፃጉዕ» (ዕዝል)* ማር ፫፤፩-፮።
ትርጉም፥ «ኢየሱስ በሰንበት መፃጉዕን አገኘው ተነስና አልጋህን ተሸከም ኃጢአትህ ተሰርዮልሃል ሁለተኛ አትበድል ከዚህ የከፋ እንዳያገኝህ አለው። መፃጉዕም ተነስቶ አልጋውንም ተሸክሞ ወደቤቱ ሄደ» ብሎ ዘመረ።

የቤት ጣራ በስተው ስለ አስገቡት በሽተኛም ሰው ዕለቱ ሰው ሰንበት ነበር ይላል ቅዱስ ያሬድ ሲዘምር ታሪኩ (ማር ፪፤፫-፲፪) ተመዝግቧል።

ጥቅስ፥ *«ሰንበት አሜሃ አመይቤሎ ለመፃጉዕ ነስቱ ጠፈረ ቤት ወአውረድዎ ኃበ ኢየሱስ ርዕዮ ሃይማኖቶ ወይቤሎ ለመፃጉዕ ተንስእ ንሣእ አራተከ»*
ትርጉም፥ «ኢየሱስ ሃይማኖቱን አይቶ የቤቱን ጠፈር አፍርሰው ወደ ኢየሱስ ያወረዱትን መፃጉዕ ኃጢአትህ ተተወልህ ተነሣ ያለበት ቀን ሰንበት ነበረ» ብሎ ዘመረ ሊቁ ያሬድ ተአምራቱን ሲያደንቅ እንዲህ ይላል።
*«ጽቡር የአውር ሕያወ ዐይነ ወውእቱሰ ወረቀ ምድረ ወገብረ ጽቡረ ወቀብኦ ዐዕይንቲሁ ለዘዕውሩ ተወልደ ወአህየዎ»* ሲተረጎም «ጭቃ ሕያው ዓይን ያውራል ጌታ ግን መሬት ላይ እንትፍ አለ ጭቃ ሠራ እውርም ሆኖ የተወለደውን ዓይኑን ቀብቶ አዳነው» አለ።

የአይሁድን ክህደትና ረብሻ የጠየቁትንም ጥያቄ እንደሚከተለው ዘምሮታል።

ጥቅስ፥ *ይቤልዎ አይሁድ በአይ ሥልጣን ትገብር ዘንተ ወይቤሎሙ ኢየሱስ አነኒ አገብር አንትሙኒ አመኑ ለግብርየ ወይቤሎሙ አነ ውእቱ እግዚአ ለሰንበት። ብውህ ሊተ እስብክ ግዕዛነ ወእክስት ዐዕይንተ ዕውራን አቡየ ፈነወኒ (መዝሙር)*
ትርጉም፥ አይሁድም በምን ሥልጣን ይህን ታደርጋለህ አሉት ኢየሱስም እኔ ተአምራት አደርጋለሁ፤ እናንተም በሥራዬ እመኑ፤ እኔ የሰንበት ጌታ ነኝ … ነፃነት ለመስበክ ስልጣን አለኝ የዕውራንን ዓይን ለመግለጥም አባቴ ላከኝ ብሎ ዘመረ።

ከዚህም ሌላ በሰንበት ባሕር መገሰፁን፤ ተአምራት ማድረጉን ማዕበል ሞገድ አውሎ፣ ነፋስ መገሰጹን፤ ታምራት መስራቱን ወዘተ አምልቶ አስፍቶ ዘምሯል።

አንባቢ ሆይ፥ በሰንበት ዕውራንን ብርሃንን በመስጠት፣ ለምጻሞችን በማንጻት፣ ሽባዎችን በማርታት አሳረፋቸው። ሰንበት የሰንበት ጌታ የሥራ ቀን ናት፣ ሰንበት ሕመምተኞች ከደዌ የሚያርፉባት የመዳን ቀን ናት፣ በመሆኑም ኢየሱስ ክርስቶስ ሰንበትን ተረጎመ እንጂ ሰንበትን አልሻረም፤ የክርስቶስ ተከታዮች የሆንን እኛም በሰንበት የታመሙትን ልንጎበኝ በወንጌል ቃል ልናጽናናቸው፣ የታሰሩትን ልንጠይቅ፣ ያዘኑትን ልናረጋጋ ይገባናል። እረፍተ ነፍስን፣ እረፍተ ሥጋን ለሰጠን ጌታ ክብር ምስጋና ይሁን። አሜን።